# ፅናት

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ልሳን

ቅጽ 1 ቁጥር 6 ቅዳሜ 7 ቀን 2002 ዓ.ም ዋጋ 2 ብር





## በውስጥ ገጾች


- ..... 3
- .. 5
- ... 6
- ... 7
- .... 8


# መድረክ በመብራት ኃይል አዳራሽ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄደ



የመድረክ የምርጫ ምልክት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ቅዳሜ ሚያዚያ 16 ቀን 2002 ዓ.ም አዲስ አበባ ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘው የመብራት ኃይል አዳራሽ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በማካሄድ ኘሮግራሙንና ዓላማውን እንዲሁም ለ2002 ዓ.ም ያቀረባቸውን ዕጩዎቹን በሕዝብ ፊት በማቅረብ አስተዋውቋል፡፡

ቅዳሜ ዕለት በመብራት ኃይል አዳራሽ የተካሄደው ብዙ ትዝታዎችን የቀሰቀሰ ነበር፡፡ ስብሰባውን የመሩት የወቅቱ የመድረክ ሊቀመንበር ኘ/ር በየነ ጴጥሮስ የሕዝቡን ባዳራሽ ውስጥ ከጫፍ እስከ ጫፍ ጥቅጥቅ ብሎ መሙላቱን በመመልከት በመግቢያ ንግግራቸው:-

«----- ሕዝባችን አዝኗል ፤ ተስፋ ቆርጧል፤ ዳግም አያንሰራራም የሚል የተሳሳተ ግምት ነበረን፡፡ የዛሬውን የሕዝብ ብዛት ሰናይ ደግሞ የነሱን / የኢሕአዴጐችን/ ተሰፋ የሚያጨልም ነው» ካሉ በኋላ ንግግራቸውን በመቀጠል « እኛም ቢሆን በየዕለቱ ባባሎቻችን ላይ የሚፈፀምባቸውን ግፍና በደል ሁሉ ተሸክመን በቆራጥነት ትግላችንን በመቀጠላችን ሕዝባችን ከኛ ጐን መሆኑ የማይካድ ቢሆንም በዛሬው ዕለት ደግሞ የበለጠ ታምር ለማየት በቅተናል፡፡ በመሠረቱ ይኸ የመብራት ኃይል አዳራሽ ታሪካዊ ነው፡፡ የዛሬ አሥር ዓመት ገደማ በአገራችን ጉዳይ በፖለቲካ ዙሪያ ስንመክር ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በክብር እንግዳነት ተገኝተው « ወይ ተባበሩ ወይ ተሠባበሩ» በማለት ታሪካዊ ንግግር አድርገው ነበር» በማለት የቆየ ትዝታቸውን አውስተዋል፡፡

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# አሁንም የሕግ የበላይነት ይከበር

## ከአንድነት ፓርቲ የተሰጠ መግለጫ

ማንም እንደሚገነዘበው የመድረክ ቁልፍ አባል የሆነው ፓርቲያችን /አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ/ በ2002 ምርጫ ላይ አመርቂ ውጤት ለማስመዝገብ በከፍተኛ ደረጃ የምርጫ ቅስቀሳ እያካሄደ ነው፡፡ በዚህ የምርጫ ቅስቀሳ ሂደት ውስጥ እያለን ከፓርቲው በከፍተኛ ዲሲፒሊን ጥሰት የተባረሩት ቡድኖች ሕገ ወጥ ስብሰባ በማካሄድ አመራር ለመለወጥና ቢሮውን ለመረከብ የሚያደርጉት አፍራሽ እንቅስቃሴ የፓርቲውንና የሐገሪቱን ሕግ እየጣሱ ይገኛሉ፡፡ አባላትና ደጋፊዎቻችን እንዲሁም አመራር አካላቱ በምርጫ ጉዳይ እና በግፍ የታሠረችውን የፓርቲውን መሪ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣን ለማስፈታት ርብርብ ደርጉበት ወቅት እነዚህ አፍራሽ ኃይሎች በተቃራኒው የመቆማቸው ጉዳይ አነጋጋሪ ነው፡፡

እነዚህ አጀንዳዎቻችን ግባቸውን እንዳይመቱ ለማደናቀፍ ሴራቸውን በማጠንጠን እንቅልፍ የሚነሳቸው ኃይሎች ትግላችን ግብ እንዳይመታ እሾህ አሜኬላ የሚፈጥረው እና ፊት ለፊት የሚታየው ተቀናቃኞችን ኢህአዴግ ይሁን እንጂ ከሱ ያላነሰ ፓርቲያችን የማዳከም ብሎም የማፍረስ ተልዕኮ ያነገቡ እንዳሉ አሁን በማያሻማ ሁኔታ እየተረዳን መጥተናል፡፡

ይህ ኃይል የሚወክለው ቀደም ሲል የፓርቲው አባላት በነበሩና የደንብ ፀር በመሆናቸው ከፓርቲው በተባበሩት ግለሠቦች ነው፡፡ ከነሐሴ 30/2001 ጀምሮ ከፓርቲው በህገ ደንብ መሠረት የተባበሩት እነዚህ ግለሰቦች አንድነትን ለማፍረስ ያልፈነቀሉት ድንጋይ ያልበጠሱት ቅጠል የለም፡፡

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ኢሕአዴግ በአልማ የድጋፍ ሰልፍ ላይ የምርጫ ቅስቀሳ በማካሄዱ ተከሰሰ

በደቡብ ወሎ ዞን ለተሁለደሬ ወረዳ ምርጫ ክልል አንድ ጽ/ቤት ሐይቅ ሚያዚያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ የኢሕአዴግን የሥነ ምግባር የደንብ ጥሰት አካሄድ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ አልማ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት መሆኑ እየታወቀ እሱ በጠራው የገንዘብ የማሰባሰብ ሰልፍ ላይ ኢሕአዴግ የምርጫ ቅስቀሳ መካሄዱን በክሱ ላይ ተመልክቷል፡፡ ሙሉ ቃሉን በገጽ 8 ይመልከቱ፡፡

# ምርጫችን በጃችን!!

# መልዕክተ ፅናት

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጥ ይፈልጋል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጥ ይፈልጋል ይሁን እንጂ ለለወጥ አልታደለም:: በየጊዜውና በየዘመኑ የለውጥ ያለህ እያለ ቢጮህም ገዥዎች ጨኸቱን ከቁም ነገር ቆጥረው አያዳምጡትም:: ባለማዳመጣቸውም በክብር ከሥልጣን ላይ ወጥተው በውርደት ሥልጣን ይለቃሉ:: ለዚህም አበው « የኢትዮጵያ ሕዝብ አቀባበል እንጂ አሸኛኘት አያው ም» ይባላል:: ኢትዮጵያውያን መሪ ያችው በሞት ሲለይ ባንዲራ ዝቅ አድርገው ስቅለው አዝነው አያውቁም::

የሩቁን ትተን ቀ.ኃ.ሥላሴ እሳቸውም ሥርአታቸውም እያረጀ በመምጣቱ ለለውጥ ዝግጁ እንዲሆኑ 53 ዓ.ም የከሸፈው የለውጥ ንቅናቄ ምልክት አሣይቷቸው ነበር:: ይሁን እንጂ የሥልጣን ጥማቸው ገና ነበርና በ13 መታቸው 66 ዓ.ም ሕዝባዊ ማዕከል ተ ቀስቅሶ እስከ ሚንስተሮቻቸው ጠራረጋቸው ፅዋ ነውና ንጉሡ መንግሥቱ ንዋይን በስቅለት ቢቀጡትም መንግሥቱ ኃ/ማርያም እሳቸውን በስውር ገድሎ ከቢሮው ሥር ቀበራቸው::

ደርግ በፋንታው በ81 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ ፍላጐቱን ምልክት አሳይቶት ነበር:: ዳሩ ግን ደርግ «የጥቂት ጀኔራሎች የሥልጣን ጥም ነው» በሚል ለጊዜው እነሱን በመግደል የለውጡን ሂደት ለማደፈን ቢሞክርም አልሆነለትም:: ብዙ ሣይርቅ ባሣፋሪ መልኩ ከሥልጣን ተወገደ::

ዛሬ በሥልጣን ላይ ያለው መንግስትም በ97 ዓ.ም የኢትዮጵያን ሕዝብ በተለመደው ጨዋነቱ የለውጥ ፍላጐቱን ምልክት አሣይቶት ነበር:: ገዥው ፓርቲ ግን እንዳለፉት መሪዎች ሀሉ እስቲ ውድቅ ደረሰ በንቀት ከመመልከት በስተቀር የለውጥ ምልክት ለማሳየት ፈቃደኛ አልሆነም:: «ልማታዊ መንግስት ነኝ እኔ ሥልጣን ከለቀኩ የተጀመሩት የመሠረተ ልማት አውታሮች ሁሉ በጀምር ይቀራሉ:: ኢትዮጵያም ትበታተናለች:: ተቃዋሚዎች አገር የመምራት ብቃት የላቸውም -----» እያለ ተፎካካሪዎቹን ጥላሸት ይቀባል:: ለመሆኑ የኢሕአዴግ መሪዎች የአገር አመራር ብቃት /ክ ሎት/ ቅብአ እግዚአብሔር ተቀብተው ነው የተወለዱት? ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንተ ወዋለን::

ለመሆኑ ለውጥ ስንል ምን ማለታችን ነው? ለውጥ ማለት ባጭር አነጋገር አሮጌውን ባዲስ መተካት ማለት ነው:: ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ሕግ በመሆኑ ይዘገያል እንጂ አሮጌው ባዲስ የመተካቱ ጉዳይ አይቀሬ ነው:: ያረጀ ልብስ ባዲስ ካልተቀየረ በስተቀር አሮጌውን ቢጠቀሙት ወይንም ቢደረቱት ተባይ ያፈራል እንጂ አይ ቅም የማዕረግ ልብስም አይሆንም:: ሌላው ቀርቶ በየዕለቱ የምንመገበው ምግብ እንደ አቅማችንና እንደ ኑሯችን ከጥራጥሬ ጀምሮ ይነስም ይብዛ የአመጋገብ ለውጥ ካላደረግን ጤንነታ ይታወካል:: ከዚህ ሀቅ ስንነሳ ሁሉም ነገር ለውጥ ያስፈልገዋል:: አሮጌውን ባዲስ መተካት የግድ ነው::

የሥርዓት ለውጥ ደግሞ ከፍ ብለን ለምሳሌነት ካቀረብናቸው እጅግ የላቀ ዋጋ አለው:: ዋጋውም በሁለንተናዊ መልኩ ወሳኝ ነው:: በመሆኑም በግዴታም ቢሆን የዘውዱ ሥርዓት በደርግ ኮሚኒስታዊ ሥርዓት ተተክቷል:: የተተካው ሥርዓት ግን የሕዝብን ጥቅምና ፍላጐት የሚያ ካ ባለመሆኑና ይልቁንም ከኢትዮጵያ ሕዝብ የረጅም ጊዜ የታሪክ ሂደትና እድገት እንዲሁም ባህልና ወግ ጋር ሊጣጣም ባለመቻሉ በፋንታው ቅጡ ባልታወቀና ይኸ ነው ተብሎ ሊጠቀስ በማይችል የኢሕአዴግ ሥርዓት ተቀይሯል:: አሁንም የኢትዮጵያን ሕዝብ ስሜት ያላረካና ለተነሱት ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ያልሰጠ መሆኑ ሕዝብ የለውጥ ያለህ እያለ በመጮህ ላይ ነው:: ኢሕአዴግ የሕዝቡን የለውጥ ፍላጐት ያጤነ በመምሰል «መተካካት» በሚል ፈሊጥ ለማምታታት ቢሞክርም ሕዝቡ ግን «ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም» እንዲሉ እንደ ውርስ እቃ ለኢሕአዴግ ልጆችና የልጅ ልጆች በቅብብሎሽ አንተላለፍም በማለት የለውጥ ያለህ እያለ ነው:: «ኢሕአዴጐች ለ18 ዓመት አይተናችኃል ይበቃችኋል:: መሽቶ ሣይጨልም በክብር ራሳችሁን ለለውጥ አዘጋጁ» በማለት የ2002 የምርጫ ውጤት ያማረ እንዲሆንና በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቁ ከወዲሁ በተለያዩ መንገዶች ሕዝቡ ድምፁን እያሳማ ነው:: ለማንኛውም የግንቦቱ ምርጫ በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅ ሁላችንም የየድርሻችንን መወጣት አለብን::

# መልዕክቶቻችሁ

**ሚያዚያ 16 ቀን 2002 ዓ.ም**

**ሕዝቡ የተሰነዘረ**

መራጩ ሕዝብ ዘንድ ለመድረክ ድጋፍ ካስገኙለ አጠቃላይ ጉዳዮች መካ ል የአሳብ ጥያቄን ማንሳቱና እንዲሁም በአጠቃላይ መገንጠልን እንደ መፍትሔ አለመወሰዱ የሚጠቀሱ ናቸው፤ ግን የመራጩን ሕዝብ ሕይወት በቀጥታ በመለወጥ ረገድ የሚያግዙ ጉዳዮችና መድረክ በብዛት ሲያነሳ አይደመጥም ለምሳሌ የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው፤ ለገበሬው በማሣው ላይ የባለቤትነት መብት እንዲ ረው ምን አሳስባችኋል::

**መልስ** :- የሕዝብ ጭሰኛ የለውም በሚል እርሶ አደሩ የመሬ ባለመብት ወይንም የይዞታ ማረጋገጫ እንዲ ረው መድረክ ማንፌስቶ በግልፅ አስቀምጧል::

**ጥያቄ** :- የደ ሶሺያሊስታዊ ርዕዮተዓለም ለሰፊው ሕዝብ ያስገኘለትና የገጠር መሬት የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች ኢሕአዴግ ከሕዝቡ እየነጠቀ አዲስ ለፈጠረው መዝበራና ሙሰና የገዥ መደብ አባላትና ለባዕዳን እየሠጠና እየቸበቸበ ነው:: ለዚህም ዓይነተኛ ምሳሌዎች ሆነው ጠቀሱ የሚችሉት በገጠር በአበባ እርሻ ማስፋፋት ሰበብ ከመሬታቸው የተፈናቀሉ ገበሬዎችና በአዲስ አበባ ደግሞ እንደ ልደታ ባ አካባቢዎች ከመሬትና ከቤት የተፈናቀሉ ዜጐች ናቸው::

**መድረክ ሲያሸንፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!!**

## መድረክ በመብራት...

(ከገጽ 4 የዞረ)

እጩ ተወዳዳሪዎቹም ከሕዝቡ ጋር ትውውቅ አድርገዋል::

የወረዳ 10ሩን ውይይት ከሌሎች ውይይቶች ልዩ የሚያደርገው መድረኩ ለሕዝብ ውይይት ክፍት የሆነው ባንድ ጉልማሣ ቀረርቶ /ሽለላ/ ነው:: እንዲህ በማለት:-

« ጎንደር፣ ትግራይ፣ ወሎ ሁሉም ወንድምሽ ነው ደቡብ ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ሁሉም ወንድምሽ ነው::

እኛ የምንሻው አንድነት በቻ ነው!! » በማለት በመ ረዋ ድምፁ ሲቀደው ሕዝቡ በጭብጨባ እድናቆቱን ችሮታል::

የዚህ የቀጨኔ ደብረ ሰላም ት/ቤት ሕዝባዊ ስብሰባም በመርቂ ሆኔታ ነው የተጠናቀቀው :: መድረክ በቀጣዮቹ ሳምንታትም ታላላቅ ሕዝባዊ ውይይቶችን ለማካሄድ ማቀዱን ለማወቅ ችለናል::

(ከገጽ 8 የዞረ)

ጸጸ

24

«

»

«

»


# ፅናት

በአንድነት ፓርቲ ኤዲቶሪያል ቦርድ የምትታተም በፖለቲካዊ፣ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አተኩራ በ15 ቀን አንዴ የምትወጣ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

አንዳርጌ መሥፍን (አድራሻ :የካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20/21 የቤት ቁጥር (አዲስ)

ስ.ቁ 0913 05-69-42

ሪፖርተር: ዳንኤል ተፈራ

ስ.ቁ :-0911 035035

የኮምፒውተር ጽሑፍ:- ትግስት ቦጋለ

ስ.ቁ 1910 142316

**አታሚ**

ሆራይዘን ማተሚያ ቤት

**አድራሻ**

ቂርቆስ ክ/ከተማ

**ቀበሌ**

17 የቤ.ቁ 124

**የአሳታሚው አድራሻ**

ቂርቆስ ክ/ከተማ

ቀበሌ 31 የቤት ቁጥር 461 ባምቢስ



# ፖለቲካ

## አምባገነን ሥርዓት በሕዝብ ድምፅ እንጂ በልመና አይወገድም

ከኢዮብ ሳለሞት

eupeqy@Gmail.com

ከታሪክ መማር ከተፈለገ ለዘመናት አምባገነኖች ስልጣናቸውን የሚለቁት በሕዝብ መራራ አመፅና ባልተቋረጠ ሰላማዊ ትግል ብቻ ነው:: በ ልና ግፍ ስቃይና መከራ ሲበዛ ሰብአዊ ፍጡር ቀርቶ አራዊትና እንሰሳትም ማመፃቸው የተፈጥሮ ህግ ነው::

ስለሆነም «እሳት ከሌለ ጭስ የለም» እንደሚባለው ኃይልና ጭቆና ከሌለ አመፅ ሊኖር አይችልም:: በመሆኑም የአመፅ ሁሉ ምንጭና ምክንያት ያው እንደሚታወቀው ጭቆና ነው:: ፍትሕ ካለ የህግ የበላይነት ከተከበረ ሙስና ካልተንሰራፋ የፓለቲካውና የኢኮሚው ስርዓት የህዝብን መብት የሚያስከብርና መሠረታዊ ፍላጐትን እንዲያረካ ሆ ከተዋቀረ ሕዝብ ከዓመፅ የሚያገኘው ጥቅም ስለሌለ ለአመፅ አይነሳም::

ህዝባችን መሠረታዊ ፍላጐቶቹ ከተሟሉለት ቅድሚያ የሚሠጠው ሠላማዊ ህይወቱን እየመራ ኑሮውን ማሻሻል ልጆቹን ማሳደግ ነው ምኞቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጀብደኝነት ብቻ ተነሳስቶ ለማመፅ የሞከረበት ወቅት የለም:: ይህን የህዝባችንን መሠረታዊ ፍላጐት ባለመረዳት ነው ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ህዝብ እየጨፈጨፈና ግፍና ስቃይ እየበዛ የሰላማዊ ትግል መሪዎችን «የጥፋት ይ » እያለ ፈረ ህዝባችንን ለዓመፅ እየገፋፋ ያለው:: አላማው ሕዝቡ በፍርሃት ተሸብሮ መድረክን እንዳይመርጥ ለማድረግ እንጂ መድረክ በሰላማዊ መንገድ የሚታገልና ለሰላም የቆመ ድርጅት ነው::

በእኛ እምነት አምባገነናዊ ስርዓት ንጉሳዊ ካባ ይጐናፀፍ ወታደራዊ ጃኬት ይልበስ እንደ ኢራን የሃይማት ካባ ይደርብ እንደወያኔ የብሔር ጥልቆ ያጥልቅ ያው ፀረ ህዝብና አፋኝ ሥርዓት ነው::

ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ሀገሩን ማዳን ታሪካዊና የብሔራዊ ግዴታ መሆኑን አውቆ ከመድረክ ጋር በመሆን የሰላማዊ ትግል መሪዋን ብርቱካን ሜዴቅሳን ለማስፈታት ከጐናችን በመቆም ታሪካዊ ግዴታውን ይወጣ::

መድረክ በሀገራችን ያለውን የተዛባ ስርዓት በመቃወም በመደ ጀታችንና በመታገላችን ነፃነት በመጠየቃችን የሀገራችን ተፈጥሮአዊ የባሕር በር ይከበር ብለን ስለጮህን « የጥፋት ይሎች» ተብለናል:: አምባገነኖች ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ለሕዝብና ለሕግ የበላይነት የሚታገሉና የሚያታግሉ ግለሰቦችን ሁሉ እንደ ወ/ሪት ብርቱካን ሜዴቅሳ ያሉትን ባላቸው አቅምና ልዩ ልዩ ስልቶች በመጠቀም ከሀገር በማስወጣት ሀገሪቱን የተማረ የሰው ኃይል ማሳጣት ነው::

ዋናው ቁም ነገር ግን እነዚህ ሆድ አደር አምባገነን ገዥዎች እስከመጨረሻው ያልተስተካከለው ነገር ቢ የሕዝብን የነፃነት ትግል ለማኮላሸት አልቻሉም:: የትግሉ መነሻ ምክንያት ቢለያይም እያንዳንዱ ትውልድ የራሱ ታጋዮች አሉት:: የዚህ ትውልድ የትግል ተምሳሌት ብርቱካን ምሳሌያችን ናት::

እኛ ኢትዮጵያውያን ለጠላት ወረራ የማንበረከክ ጠላትን አዋርደን ወደ መጣበት የመለሰን መሆናችንን ታሪክ ቢመሠክርልንም የራሳችንን አምባገነን ገዢዎች ለመቋቋም ባለመቻ ላችን ለተሾመው መገዛታችንና ላበላን በማደግደ ለጨ መሪዎች መሣሪያ በመሆን ህዝባችንን ማስጠቃት ማዳችን ሆ ለውጭ ጠላት አይበገሬ ብንሆንም የቤት ውስጥ ገዥዎ ቻችንን ለመቃወም ድፍረትና ወኔ የለንም 18 ዓመት ግፍና በደል ሲሠራብን አሻፈረኝ ማለት አቅቶን በለቅሶና በዋይታ ኖረናል:: ስለሆነም ይህን ተግባራችንን አቆመን ሀገራችን የጋራ መሆኑን ተ ረድተን ግንቦት 15 ቀን ለመድረክ ድምፃችንን በመስጠት ሰብዓዊ ክብራችንና ዜግነታችንን እናስመልስ::

## ጥይት ራሱ ገድሎ ራሱ ይጮሃል!

ሕውሓት ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ እግሩን አፈራጦ ከተቀመጠበት 1983 ጀምሮ እስካሁን ድረስ ማ ለብኝነት የሕዝብ ሉአላዊነት በእጅጉ እ ረገጠ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ከህውሃት ኢህአዴግ የጭቆና አገዛዝ ነፃ ለመውጣት በነበረው ታላቅ ምኞትና ፍላጐት 1997 ግንቦት በተካሄደው ሶስተኛ ዙር ምርጫ ጫፍ እስከ ጫፍ ተንቀሳቅሶ ያሳየው ህዝባዊ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ምን ይመስል እንደነበር እንኳንስ እኛ የችግሩ ተሸካሚዎች ቀርቶ መላው ዓለም ሕዝብ የሚያስታውሰው ነው:: ታዲያ ከእኔ ወዲያ ለሣር ብሎ የተነሳው ገዥ መደብ ያን የሕዝብ ፍላጐት በጉልበቱ ጨፍልቆ ሥልጣን ኮርቻ ላይ ላለመውረድ ያደረገው መንፈራግጥና መወራጨት ከሕዝባችን ህሊና ውስጥ በቀላሉ የ የስንት ወገ ችን ደም በየ አስፋልቱ እንዳልፈሰሰ የሕዝብ ሀብትና ንብረት በሆነው ቴሌቪዥን ሬዲዮና ጋዜጣ አይን ያወጣ ውትወታና ለ ፋ በማካሄድ ላይ ይገኛ ል::ሕውሓት ኢህአዴግ የጫካ አንባሳ ዛሬም በመህል አገርና በየትኛውም አቅጣጫ ለሆዳቸው ያደሩ ተለጣፊዎቹን አሰማርቶ ምን

በማድረግ ላይ እንዳለና ምንስ እያካሄደ እንደሆነ ሕዝባችን መላው ዓለም የ ያውቀው ነው:: አንዴ «ዴሞክራሲያዊና ልማታዊ መንግስት ነፃ ፍትሃዊና የሕዝብ ተአማኒነትን የሚያገኝ ምርጫ ለማካሄድ ተዘጋጅቻለሁ» ሌላ ጊዜ «ተቃዋሚዎች ሀገር ሊመሩ እርስ በራሳቸው መስማማት ያልቻሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቀም አንዳችም እርባና ያለው ፕ ሮግራምና አላማ የሌላቸው ናቸው::» በማለት የጥላቻ ዘመቻ ያካሄዳል:: ኢህአዴግ የተለመደ ልቅ ፕ ሮፖጋንዳውን ሲነዛባቸው ሕዝብ እየሰማ ይታዘባል:: አረ ለመሆኑ ኢህአዴግ በቁጥጥሩ ስር ያሉትን ሚዲያዎች ለሕዝብ ጠቀሜታ ያለው አስተማሪና ቁም ነገር ለማስተላለፍ ብቃቱስ ተፈጥሮው መች ይፈቅዱለትና? ለተቃዋሚውችስ መቼ እድል ሰጣቸውና ነው ዓላማቸው ራእያቸውን ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ ምን ማድረግ እንዳሰቡ ከሕዝብ ጋር ተገናኘ ለመወያየትና በቂ የሚዲያ ሽፋን ሣያገኙ አማራጭ የላቸውም እንዲያውም ጭፍን ተቃውሞ ብቻ ነው የሚያሰሙት የሚለን በሌለ በኩል በአለፈው የ1997 ምርጫ ወቅት ባሸነፉባቸው ክልሎች መች የማስተዳደርና አመራር

የመስጠት አድሎ ነው ብቃታቸውንም ሆነ ድክመታቸውንም በሕዝብ ለማስመዘን የቻሉት?

በተፈጥሮ ባገኘ ው ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታችን ተጠቅመን በድምፅ አሸናፊነታችን ማረጋገ

ምርጫ ቅስቀሳ የአንበሳውን ድርሻ በመያዝ የሕዝብ ተሳትፎ በሌለበት ስቱዲዮ ውስጥ በር ዘግቶ በራሱ ጋዜጠኞች አወያይነት ቀራፂነትና አስተላላፊነት ያልፈለገውን ቆርጦ የሚ ውን ቀጥሎ በማቅረብ አደናጋሪ ሁኔታዎችን በማራመድ ላይ ይገኛል:: ይህ አካሄድ እስከመች ነው የሚቀጥለው? ሀሳብን የመግለጽ የመቃዎምም ሆነ የመደገፍ እድል የ ገኘው መች ነው? እስከዛሬ ኢህአዴግ የልመና ስልቻውን ይዞ በአውሮፓ በአሜሪካና በኢስያ በሕዝብ ስም የሚያመጣው የእርዳታና የብድር ገንዘብ የነፍስ አድን እህልና መድሀኒት ለህዝብ ጥቅምና አገልግሎት ሳያውል ትንሽ ትንሽ አንጥብጣቢ የአስፋልት መንገድ የአየር ማረፊያ የትምህርት ተቋማት ሆስፒታሎች ጤና ጣቢያዎች ወዘተ ------- ሠራሁላችሁ /ገነባሁላችሁ/ በማለት ሕዝብን እያታለለና በንቀት ላይ የተመሠረተ ተልዕኮውን እያራመደ እስከመቼ እንዲቀጥል እንፈቀድለታለን?

በብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ስም እየነገደ 17 ዓመት የታገልኩትና ጦረኛውን ደርግ ያስወገድኩበት ለእናንተ ነው ያለ እኔ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንደ ሀገር አትቀጥልም መ ር ከፈለ እኔ ያልከ ን ብቻ ሆ ነ እያለ የሚነዛው ፕሮፖጋንዳ እስከ መቼ ተሸማቀንና የትራንስፖርት ርሀብ እንግልት አፈናን ጭቆና አሜን ብለን ተቀብለን እንገፋለን? ቢያንስ እንደሱ ጫካ ገብተን ነውጥ አንግበን ደም አፍስስን በኃላ ቀር የትግል ዘዴ ታግለን ለድል ባንበቃ በተፈጥሮ ባገኘ ው ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብታችን ተጠቅመን በድምፅ ንፍገት አሸናፊነታችን ማረጋገ ይ ብናል በተባበረ የሕዝብ የመምረጥ መብት ለአንዴ ለመጨረሻ ጊዜ ልናስወግደው ይገባል::

# መድረክ በመብራት ...

(ከገፅ 1 የዞረ)

የመድረኩ መሪ ወ/ሮ ላቀች ደገፉ የኘ/ር በየነን ትውስታ መስረት በመድረክ የራሳቸውን ትውስታም በመሀሉ ጣል አድርገዋል::« ከዚህ አዳራሽ ከዚችው መድረክ ሌላም ታሪክ ተከናውኖ አልፏል:: ይኸውም በ2001 ዓ.ም ህዳር 27 ቀን የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት ይሆናል ብለው ያልጠበቁት ሕዝብ ካዳራሹ ተርፎ ግቢውን በመሙላቱ ወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ በዕድሜ ልክ እሥራት የታጨችበት ዕለት ነበር» በማለት ከገለፁ በኋላ መድረኩን እንደገና ለኘ/ር በየነ ጴጥሮስ ለቀዋል::

ኘ/ር በየነ በንግግራቸው ውስጥ ብዙ ቁም ነገሮችን አስጨብጠዋል:: ጥቂቶቹ « ---- የኢሕአዴግ ካድሬዎች በየቤቱ እየዞሩ የምረጡኝ ዘመቻ በሚያካሄዱበት ወቅት መራጩን ሕዝባችን አንድ ላምስት በሚሉት የጥርነፋ ሥርዓት ጠርንፍው « እኛን ካልመረጣችሁ » እያሉ በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እየደለሉ ነው:: እኛ በአዳራሽ ውስጥ ሕዝባችንን ጠርተን በግልፅ እንወያያለን እንጂ መደር ለመንደር እየዞርን « እኛን እንድትመርጡ ፈርሙ» እያልን ሕዝባችን ግራ አናጋባም ወይንም ስንዴ ልንሰጥ ነውና ተሰብሰቡ ብለን አን ም» በማለት ሲናገሩ ሕዝቡ በሣቅና በጭብጨባ አጅቧቸዋል::

ኘ/ር በየነ ጵጥሮስ ሕዝባቸውን በድጋሚ ሲያሞግሱ እንዲህ ብለዋል« ዛሬ ገዥው ፓርቲ እኔን ያየህ ተቀጣ በሚያስመስል በግልፅም ሆነ በሥውር በሕዝባችን ላይ በሚካሄደው ዛቻና መሥፈራራት ሣትበገሩ ወደ አዳራሹ ተማችሁ የመምጣታችሁ ጉዳይ የሚያስመሰግናችሁ ቢሆንም የአዲስ አበባ ሕዝብ ለውጥ ፈላጊና አሻፈረኝ ባይ ለመሆኑ በቂ ማረጋገጫ ነው» ካሉ በ_ላ « ወገኖቸ ከእንግዲህ መድረክ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት አሣልፎ ላለመሥጠት ቆርጦ ተነሥቷል» በማለት ሲናገሩ የሞቀ ጭብጨባ ከሕዝቡ ተችሯቸዋል:: ንግግራቸውን በመቀጠል « የመድረክ እንቅስቃሴ በጥላቻና በቂም በቀል የተመሠረተ አይደለም:: ጥያቄው ሕዝብ ለውጥ ይፈልጋል መብቱ ይከበርለት ነው እያልን ያለነው:: የተበላሹ ነገሮች አሉ፤ በአገር ሉዓላዊነት ላይ፤ በዜጐች ዙሪያ የከፉ ችግሮች አሉ:: እነዚህ መቀጠል የለባቸውም አልን እንጂ ኢሕአዴግን ብቻ በጥፋተኝነት በመወንጀል ጠብ ያለሽ በዳቦ አላልንም» በማለት በየነ ጴጥሮስ የመግቢያ ንግግራቸውን እንደ ጨረሱ በኘሮግራሙ መሠረት ቀጣይ ተራ የእጩዎች ማስተዋወቅ ስለነበር የትምህርት ደረጃቸውንና የሥራ ልምዳቸውን አስተዋውቀው ከጨረሱ በኃላ ከሕዝቡ ጋር በቀጥታ ውይይት ተጀመረ::

አንዱ አዛውንት ተነስተው መምህር እንደሆኑ ራሳቸውን ካስተዋወቁ በኋላ ሶስት ልጆች እንዳሏቸው ጠቅሰው የመጨረሻ ልጃቸው ሴት እንደሆነችና በዛሬው እለት ኢሕአዴግ ስብሰባ እንደጠራት ስትነግራቸው « አባ ለምን እንደምሄድ ታውቃለህ? 25 ብር ስለሚሰጡኝ ለካርድ መግዣ አንተን እንዳላስቸግርህ ብዬ ነው» በማለት ሲናገሩ ተሰብሳቢውን ሕዝብ አስቀዋል:: ሌላው ተናጋሪ ቄንጠኛ ኬፓቸውን ወደ አፍንጫቸው ዝቅ አድርገው « ባለፈው በተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሣ ጠ/ሚኒስትሩን « ሥልጣነዎን መቸ ነው የሚለቁት» በማለት ላቀረቡላቸው ጥያቄ የሰጡት መልስ በመተካካት እንደሚለቁ ጠቅሰው መጭውን አምስት አመት ግን በሥልጣን ላይ እንደሚቆ ግልፅ አድርገዋል:: ለመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ዕቃ በመተካካት በሚል ፈልጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ በውርርስ ሊተላለፍ ነ ? ሥልጣናቸው በዘር እንዲተላለፍ ከፈለጉ ለምን ዘውድ አይጭኑም » ሲሉ ሕዝቡ « ማሽላ ሲያር ይስቃል» እንዲሉ አውክቶ በመሣቅ በጭብጨባ አድናቆቱን ገልፃላቸዋል::

ሌላው ተናጋሪ በቡኩላቸው የተሰብሳቢውን ሕዝብ ስሜት ስቅቅ በሚያደርግ መልኩ ተናግረዋል:: እንዲህ ነበር ያሉት « በ97 ምርጫ አንዲት እናት ሁለት ልጆቻቸው ከቤታቸው በር ተገደሉባቸው:: እናትም ልጆቻቸውን ቀብረው የልጆቻቸውን ሀዘን ተሸክመው መፅናናት አልቻሉምና በሶስተኛው ቀን ራሳቸውን ገደሉ:: ኢሕአዴግ በ2002 ዓ.ም እንዲህ አይነት ድርጊት ላለመፈፀሙ ምንም አይነት ዋስትና አልሰጠም:: እን ያውም ተመሣሣይ ድርጊት መፈፀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲዝት ይደመጣል:: ካድሬዎቹም በሕዝቡ ላይ ወከባ እያካሄዱ ናቸው:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ከእንዲህ ዓይነት አሣፋሪና ወረዳ እርስበርስ ከሚያናክስ ሥርዓትና አመራር ይገላግልሽ በሏት » ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል:: በተረፈ ስለባህር በር፣ ስለመድረክ ጥምረትና መርህ፣ ስለኒኦ ሌበራሊዝም ፣ ኢሕአዴግ ቢሸነ ሥልጣኑን በሰላማዊ መንገድ ያስረክባል ወይንስ አያስረክብም? የመሣሰሉት ጥያቄዎች ተሰንዝረው በቂ መልስ ከመድረኩ ተስጥቶባቸዋል:: በዚህም የስብሰባው ፍፃሜ ሆኗል::

በሌላ በኩልም በዚሁ ዕለት ከሰዓት በፊት በወረዳ 24 በ01/05 ቀበሌ አዳራሽ መድረክ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሄዷል::

በሌላ በኩል ወደ አማራ ክልል ሰሜን ወሎና ደቡብ ወሎ ዞን ያቀናው የመድረክ አንዱ አካል የሆነው የአንድነት ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አባላት አራት የተሣኩ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን አካሄዶ መመለሱን አረጋግጧል::

የቡድኑ አባላት የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ የተከበሩ አቶ ተመስጌን ዘውዴ ፣አቶ አሥራት ጣሴ ፣ አቶ አንዱዓለም አራጌና ወጣት ዳንኤል ተፈራ ናቸው:: አራቱ ሕዝባዊ ስብሰባዎች እጅግ የተሣኩና አመርቂዎች እንደነበሩ የቡድኑ አባላት ገልፀው፤ ቡድኑ በመጀመሪያ ስብሰባውን ያካሄደው እሁድ ሚያዚያ 17 ቀን 2002 ዓ.ም ደሴ ከተማ የባህል ማዕከል ሲሆን ከ3 -7 ሰዓት ድረስ በተረጋጋና ጨዋነት በተላበሰ መልኩ ስብሰባው እንደተጠናቀቀ ገልፀዋል::

ቡድኑ በማግስቱ ሰኞ ሚያዚያ 18 ቀን ወደ ሰሜን ወሎ በማቅናት በወልደያ ከተማ ከ3 - 7 ሰዓት ድረስ በተመሣሣይ ሁኔታ ሕዝባዊ ውይይት አካሂዶ ተመልሷል:: እንዲሁም ማክሰኞ ሚያዚያ 19 ቀን በኮምቦልቻ ከተማ ከ 3- 7 ሰዓት ድረስ ሕዝባዊ ውይይት ያካሄደ ሲሆን ያኑ ዕለት በከሚሴ ከተማ በመገኘት ከሰዓት በኋላ የመጨረሻውን ሕዝባዊ ውይይት አካሄ ወደ አዲስ አበባ ተመልሷል::

ከዚህ አዲስ አበባ ደግሞ ቅዳሜ ሚያዚያ 23 ቀን 2002 ዓ.ም መርካቶ በስኒማ ራስ አዳራሽ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ እስከ 11:30 ድረስ እጅግ የሞቀ ሕዝባዊ ስብሰባ የተካሄደ ሲሆን አዳራሹ ሞልቶ ሊይዘው ከሚችለው በላይ በመሆኑ ብዙ ሕዝብ በዘበኞች ወደ ውስጥ እንዳይገባ መታገዱን ለማስተዋል ችለናል::

የዕለቱ የክብር እንግዳ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ሲሆኑ በመግቢያ ንግግራቸው « ኢሕአዴግ መድረክ የሥነ ምግባር ፊርማ አልፈርምም ስብሰባ ረግጦ ወጥቷል እያለ ይወነጅለናል:: ለሕዝባችን የማይጠቅም፣ ፓርቲያችን የሚጎዳ ከሆነ ወደ ፊትም ቢሆን ኢንፈርምም ፤ ስብሰባም ቢሆን አቋርጦ የመውጣት መብታችን የተጠበቀ ነው» ካሉ በኋላ «አንድ ምሳሌ ልጥቀስ ጠ/ ኮፓን ሃገን በተካሄደው የመሪዎች ጉባኤ የአፍሪካን ጥቅም የማያከብር ከሆነ ስብሰባውን ጥለ
በማለት ተናግረው ነበር:: የሳቸው ሲሆን ትክክል የኛ ሲሆን ወንጀል የሚሆንበት ምክንያት አይገባንም» በማለት ሲናገሩ ታዳሚው በጭብጨባ አድናቆቱን ገልጾላቸዋል::

ከኢ/ር ግዛቸው የመክፈቻ ንግግር በኋላ እጩ ተወዳዳሪዎች ለሕዝቡ ራሳቸውን አስተዋውቀዋል:: ቀጥሎ ደግሞ በኘሮግራሙ መሠረት መድረኩ ለሕዝብ ውይይት ክፍት ሆኖ በርካታ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ተሰንዝረዋል:: ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ከክብር እንግዶች መሀከል አንዱ ነበሩና ኢሕአዴግን በተመለከተ ለተሰነዘሩት ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ:-

« ሰሞኑን በምኖርበት አካባቢ ኢሕአዴግ የለጠፋቸውን ፓስተሮች ተጠግቼ ሳነባቸው የተጀመረውን የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ሂደት ማስቀጠል ኢሕአዴግን ምረጡ! ይላሉ:: የነዚህ ፓስተሮች መልዕክት ግልፅ ነው:: ኢሕአዴግ ልማትን እንደ መያዣ እየተጠቀመበት መሆኑን ነው:: ኢሕአዴግ ካልተመረጠ የተጀመሩት ልማቶች ሁሉ እንደ ተጀመሩ ይቀራሉ ማለት ነው:: ኢሕአዴግ ልማታዊ መንግስት ነኝ ሲልም ይደመጣል:: ጥሩ ነው አዲስ አበባ ውስጥ መንገዶች ተሠርተዋል:: የማን እንደሆኑ ባናውቅም ረጃጅም ፎቆችም እየተገነቡ ናቸው:: እነዚህ ግን በቂ ናቸው ማለት አይደለም:: በመሠረቱ የመንገዶች መሠራትና የፎቆቹ መገንባት በራሳቸው ነፃነት ሊሆኑ አይችሉም:: ነፃነት ከሌለ የሕንፃዎቹ መገተር ትርጉም የለውም:: ቁሳዊና መንፈሳዊ ነፃነቶች በመጀመሪያ መረጋገጥ አለባቸው:: ኢሕአዴግ ደግሞ ነፃነት ሊያረጋግጥ አይችልም:: አሥራ ዘጠኝ ዓመት አይተነዋል:: ያለ ዕቅድ መንገዶችን ይቆፍራል፤ ቤቶችን ያፈርሳል:: እኔን ካልመረጣችሁኝ እነዚህ ሁሉ ተጀምረው ይቀራሉ ይለናል» በማለት ሲናገሩ ሕዝቡ በሳቅ በማውካት በጭብጨባ አድናቆቱን ለግሷቸዋል::

ከዶ/ር ኃይሉ ንግግር ቀጥሎ ዶ/ር ነጋሶ፣ አቶ ተመስጌን ፣ አቶ አንዱዓለም አራጌና ሌሎቹም ንግግር አድርገዋል:: ከሕዝቡ የሚሠነዘሩት አስተያየቶችና ጥያቄዎች አመርቂዎችና አወያይዎች ስለነበሩ ያላንዳች መሠልቸትና መድከም እስከ መጨረሻው ሰዓት ድረስ ውይይቱ ባማረ ሁኔታ ተካሂዷል::

በተመሳሳይ ሁኔታ በማግስቱ እሁድ ሚያዚያ 24 ቀን 2002 መድረክ በወረዳ 10 ቀጨኔ ደብረ ሰላም ት/ቤት አዳራሽ ከጧቱ 3 - 7 ሰዓት ሕዝባዊ ውይይት አካሄዷል:: የዕለቱ የክብር እንግዳ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ሲሆኑ በመክፈቻ ንግግራቸው ወቅት እንዲህ ብለዋል:-

« የወረዳ 10 ሕዝብ ባለውለታዬና ያኮራኝ ሕዝብ ነው:: የማመስገኛ የጊዜና የቦታ አጋጣሚ አጥቼ እስካሁን ድርስ ቆይቼ ነበር:: ዛሬ በዚህ አጋጣሚ በመሀከላችሁ ተገኝቼ ለማመስገን እድል በማግኘቴ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ» ካሉ በኋላ « እግዚአብሔር ያክብራችሁ:: የዛሬ 5 ዓመት አኩርታችሁኛል:: የኢሕአዴግን ተወዳዳሪ 30 ሺ ለ 3 ሺ ያሸነፍኩት በወረዳ ነው:: በዚህ ዓመት ደግሞ ለኔ ያደረጋችሁትን ድጋፍ ለአቶ ተክሉ ሸዋ እንደምታደርጉለት ሙሉ ተስፋ አለኝ:: በተረፈ አመሰግናለሁ» በማለት ንግግራቸውን ሲቋጩ ሕዝቡ በበኩሉ አክብሮቱን በጭብጨባ ገልጾላቸዋል::

ከዶ/ር ኃይሉ የመክፈቻ ንግግር በኋላ ዶ/ር ነጋሶ፣ አቶ ተመስጌን ዘውዴ፣ አንዱዓለም አራጌና ሌሎቹም ንግግር አድርገዋል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

# ካስተዋልነው ?

ከአ.መ

« !
»
«
»
/ «
! »
«
»
/ / 199 .
« /
! » « » «
( ) »
«
/ »
/ «
« !»
»
66 . . . !»
« »
« » 2 2
« »
/
«
»
« !
…!»
/

- « ወይ! በሰማም! ምን አይነት አስቀያሚ ነሽ! እኔ አንቺን ብሆን ገበያ አልወጣም ነበር» አለች ይባላል።

/

« ! !
» « /
? ?»
/
/
« !»
/
-
! !!

ወደ ገ 8 ዞሯል

